# አንድነት ሰሜን አሜሪካ የድጋፍ ድርጅቶች ማሕበር

**ANDINET NORTH AMERICA ASSOCIATION OF SUPPORT ORGANIZATIONS (ANAASO)**

1334 9th Street, NW. Suite # 1 Washington DC. 20001.
Tel: (202) 462 0556 Fax: (202) 462 0557 Email: info@andinetusa.org


# የጥላሁን ጥላ

ሚያዝያ 25 ቀን 2001 ዓ.ም

መላው የኢትዮጲያ ህዝብ ከልቡ የሚያደንቀውንና በፈቃዱና በውዴታውም «የሙዚቃ ንጉሥ» ተብሎ የተሰየመውን የአርቲስት ዶክተር ጥላሁን ገሠሠን ከዚህ አለም መለየት ዜና የሰማነው በከፍተኛ ድንጋጤ ነው:: እኛ በሰሜን አሜሪካ የምንገኝ የአንድነት ፓርቲ ደጋፊዎች ለሙዚቃው ንጉሥ ቤተሰቦች የእግዚአብሄር ያጽናችሁ መልዕክት ስናስተላልፍ በአገራችን ምድር ተገኝተን ተወዳጅ የህዝብ ልጅ የሆነውን ጥላሁንን አፈር የማልበስ ዕድል ባለማግኘታችን በፀፀትና በንዴት ተቃጥለን ነው::

ጥላሁን ባለፉት 50 ዓመታት ለዘመናት በማያረጁ ድንቅ ዘፈኖቹ አዲሱን ትውልድ ከአሮጌው ትውልድ ያስተሳሰረ፣ ሀገራዊነትን ያሰረፀ ፣ የአንድነታችንን ድርና ማግ ያጠበቀ፣ በአያሌ ዘፈኖቹም የአፄውን የደርግንና የወያኔን ስርአት ያጋለጠ፣ ሌላው ቀርቶ በአሁኑ ወቅት ያለውን የፖለቲካና የፖለቲከኞች ሁኔታ በትንበያ መልክ የዘፈነ ነው:: «እንደ ወንዝ ድንጋይ አሣ እንደላሰው፣ ሙልጭልጭ እያለ አስቸገረ ሰው» ነበር ያለዉ።

- «ውረድ በለው ግፋ በለው ...» እያለ፣ የአገሩን ድንበር ለማስከበር የዘመተውን ሠራዊት ሲያነቃቃ የነበረው ጥላሁን የታሪክ ምፀት ሆኖ ድንበር ያስገፉና ድንበር ያስቆረሱ ወያኔዎች «ድንቅ የህዝብ ልጅ» ብለው በርካሽ የፖለቲካ ፕሮፓጋንዳ ብሔራዊ የአቀባበር ስርአት ሲያስደርጉለ ት ማየት ምንኛ ያስቆጫል!!

- ጥላሁን ባልወልደውም የመንፈስ ልጄ ነው ብሎ የመሰከረለትን ቴዲ አፍሮን በእስር ላይ እያማቀቀ ያለው ወያኔ፣ በአባቱ ቀብር ላይ ልጁ እንዳይገኝ ማድረጉ፣ ጭካኔውንና ኢትዮጵያዊ ባህል አልባነቱ በግላጭ የሚያሳይ በመሆኑ፣ የጥላሁንን ሞት የህዝብን ፍቅር መግዣ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በአፅንዖት የምንቃወመው ነው።

- እኛ የአንድነት ደጋፊዎች፣ የጥላሁንን ፍቅር ከህዘባችን ፍቅር ነጥለን አናየውም። ይልቅስ እንደ ነፍስና ስጋ የተጣመሩ ናቸው እንላለን:: ለዚህም ነው የጥላሁንን «ዋይ ዋይ ዋይ

ሲሉ፣ የረሀብን ጉንፋን ሲስሉ» የሚለውን ዘፈን ዛሬም ስንሰማ በወያኔ አገዛዝ ስር በረሀብ የሚማቅቁና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወገኖቻችን ከፊታችን የሚመጡት። ወያኔንም ለመጣል ያለንን ቁርጠኝነት አድሶ ጥላሁንን የሚወድ ሁሉ የጥላሁን ጥላ ያርፍበታል የሚል ፅኑ እምነት አለን።

- «ምግብማ ሞልቷል አምላክ የሰጠን ፣ የፍቅር ረሀብ ነው እኛን የጎዳን » ብሎ የዘፈነው የሙዚቃ ንጉሥ **ፍቅርም ምግብም** ከሀገራችን ጠፍተው ባሉበት ወቅት ከመሀላችን ቢለይም፣ ለሰው ልጅ እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ፍቅርና ምግብ ለማስገኘት የምናደርገውን ተጋድሎ በሞቱ ማግሥት በማደስ በጥላሁን ጥላ ስር እንውላለን።

- ተተኪ የለሹና ወደር የለሹ የሙዚቃ ንጉሥ ጥላሁን «ሀላፊ አግዳሚውን በመጠቀምሽ፣ ሌባ ጣት እያሉ ስም አወጡልሽ...» በሚለው አስተማሪ ዘፈኑ አንዱ ጣት ወደ ሰው ሲያመለክት ሶስቱ ወደ ራስ እንደሚጠቁሙ ያስተላለፈውን ትምህርት ዛሬ በሞቱ ማግስት፣ ጥላው ያረፈብን ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ቆርጠን ብንነሳ «ዕድፍ ሆነው እንዶድ ነን» የሚሉትን ዞር በሉ ማለት ብንጀምር፣ ለጥላሁን ወያኔያዊ የአዞ እንባ ሳይሆን በተግባር የሚተረጎም የፍቅር እዳ መክፈላችን ነውና እሰዬው ያስብላል ብለን እናምናለን።

- ዛሬ የኢትዮጲያ ህዝብ መገመት በሚያስቸግር ሰቆቃ ላይ ይገኛል። እንደ ጥላሁን ሀገራዊ ስሜትን በህዝብ ዘንድ ያሰረፀው፣ ኢትዮጲያዊነት ዳግም እንዲንቦገቦግ ያደረገው፣ አንጋፋዉና ትንሹ ጥላሁን ገሠሠ፣ ቴዲ አፍሮ፣ በእስር በመማቀቅ ላይ ይገኛል። የህግ የበላይነት እንዲከበር ሰቆቃና ግፍ አክትሞ፣ ሰላም ፍቅር የሰፈነበት አንድነት የፀናበት ስርአት እንዲሰፍን የምትታገለዉ፣ በቂምና በጥላቻ ካልተነካካው አዲስ ትውልድ የፈለቀችው መሪያችን ብርቱካን ሚደቅሳ በቃሊቲ ትገኛለች። ወያኔዎች በዘር በሀይማኖት መከፋፈል እያመጡና የተለያዩ መሰሪ መንገዶች እየተጠቀሙ የህዝብን ፍቅር ለማግኘት አልቻሉም። የጥላሁን ጥላ ያጠላበት በዚህ የሀዘን ወቅት «እስከ መቼ ከአንቺ ጋር እኖራለሁ፣ አልቻልኩም መረረኝ ብያለሁ» የሚለውን ማንጎራጎሩ ግድ ነው።

- ጥላሁን የህዝብ ልጅ በመሆኑ የህዝብ ፍቅር የተቸረው ነው። በዚህ የሀዘን ወቅት ለቤተሰቦቹ መፅናናትን እንዲሰጥልን ፈጣሪያችንን እየለመንን በተላበስነዉ የጥላሁን የአገር ፍቅር ጥላ ስር ሆነን «ግፉ በለው» በማለት እያዜምን፣ ትግላችንን በአባቶች ወኔ ከግብ እንደምናደርሰው ቃል ስንገባ የጥላሁን ሀዘን ከልባችን እንደገባ ዋና መግለጫችን ነው።

የሰሜን አሜሪካ የአንድነት ድጋፍ ድርጅቶች ማህበር